# በምንቆጥበው ገንዘብ ያልተቆጠበ ልማት

ቻላቸው ከዓለም ገና ቀበሌ 02

ኢትዮጵያ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሃብቷ፤ በታሪኳ በተለይም ነጻነቷን በውጭ ወራሪ ኃይሎች ባለማስደፈሯ፤ የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት እና የበርካታ ባህሎች ባለቤት በሆኑ ብሄር ብሄረሰቦች መኖሪያነቷ፤ በሰው ዘር መገኛነቷ ወዘተ ትታወቃለች፡፡ በጥንታዊ ታሪኳና ሥልጣኔዋ የምታወቋን ያህል ግን አሁን ካደጉት ሃገራት ተርታ እጅግ ወደ ኋላ የቀረች መሆኗ የቀደመውና የዚህ ትውልድ ባጠቃላይም የዜጎቿ ሁሉ የዘመናት ቁጭት ነው፡፡

ተነሰራፍቶ ለኖረው ድህነታችንና ኋላ ቀርነታችን የየራሳቸው ባህሪያት ያላቸው በርካታ ምክንያቶችን ማዘርዘር ቢቻልም፤ በዋናነት ግን በተለያዩ ወቅቶች በኢትዮጵያ በተፈራረቁ ፊውዳላዊ፤ ጨቋኝ፤ አምባገነናዊና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ሥርአተ መንግሥታት የተነሳ በተፈጠሩና በተባባሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ምክንያት እንደሆነ መጠቆም ይቻላል፡፡ ከዘመናት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በላያቸው ላይ ከዘመናው የጭቆናና አፈና አምባገነናዊ አገዛዝ ተላቀው የሕዝቦች ዴሞክራሲያዊና የእኩልነት መብት የተረጋገጠበትን ሥርአት እውን ማድረግ ችለዋል፡፡ በዚህም ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጀምሮ ሃገሪቱ በአዲስ አይነት አስተሳሰብና ዴሞክራሲያዊ ሥርአተ በመመሥረት ተጭኖባት ከነበረው ድህነትና ኋላ ቀርነት ለመላቀቅ በሚያስችላት የእድገት አቅጣጫ ጉዞ ጀምራለች፡፡

ኢትዮጵያ ተፈጥሮ በለገሳት ሃብትና ጸጋ ተጠቅማ በዜጎቿ ጥረት ለመልማትና ለማደግ ሳትችል ከመቆየቷም በላይ ሕዝቦቿን እንኳ ለመመገብ ተስኗት ለተመጽዋችነት የተጋለጠችበት አሸማቃቂ ክስተት ጠባሳው ያልሻረና አሁንም ድረስ ከችግሩ ያልተላቀቀችበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ይህን ሁኔታ ለማለወጥና ልማትን በማፋጠን የዜጎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥም መንግሥት ሰፊ የማስረተ ልማት እቅድ ነድፎ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ልማትን ለማፋጠንም በዋናነት ሰፊ የማስረተ ልማት አውታሮችን ማዘርጋትና ማስፋፋት ግድ ይላል፡፡

በዚህ ረገድም ኢትዮጵያ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የመንገድ፤ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ፤ የቴሌ እንዲሁም የተለያዩ የማህበራዊና የማስረተ ልማት አውታሮች ግንባታና ማስፋፋት ሥራዎችን በስፋት በማካሄድ ላይ ትገኛለች፡፡ በየዓመቱ ከፍተኛ እሮርታ እያሳዩ የመጣውን የሃገሪቱን ኢኮኖሚያዊ

እድገት ተከትሎ የኃይል አቅርቦት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህም ፍላጎት በቀጣዩቹ ዓመታት ይበልጥ እየጨመረ እንደሚሄድ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ/2003-07/ መሰረት የሃገሪቱን ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም እስከ 10ሺህ ሜጋዋት ለማሳደግና ተደራሽነቱንም ወደ 75 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ ቀደም ሲል ሥራቸው ተጠናቆ አገልግሎት ማስጠት ከጀመሩት የኃይል ማመንጫ ግንባታዎች በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት የነፋስና የጂኦተርማል ኃይልን ጨምሮ ሌሎች ግዙፍና መካከለኛ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከግዙፍ ግንባታዎች መካከልም የግቤ ሦስት እና ከወራት በፊት የሥራው መጀመር በይፋ የተበሰረለትና በዓባይ ውሃ ላይ የሚገነባው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በተለይም የህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ታላቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡

የዓባይ ስም በተነሳ ቁጥርም የኢትዮጵያ፤የግብጽና የሱዳን ስም አብሮ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ዓባይ ከምንም በላይ ሦስቱን ሃገራት የሚያስተሳስር ከመሆኑና በይበልጥም ለግብጽና ለሱዳን የህልውናቸው፤የታሪካቸውና በተለይም ለግብጾች የጥንታዊ ሥልጣኔአቸው መሰረት ተደርጎ የሚታይ በመሆኑ፤ለዘመናት የመላውን ዓለም የታሪክ ተመራማሪዎች ቀልብ ገዝቶ የኖረ ታሪካዊ ወሃ ነው፡፡ እስካሁን በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ላይ ከተደረጉ እጅግ በርካታ ልዩ ልዩ ጥናቶችና ታሪካዊ ዳሰሳዎች መካከል በዓባይ ላይ የተደረገውን ያህል በማንም የምድራችን ወንዝ ላይ እንዳልተደረገ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ለዓባይ /ናይል/ አስተዋጽኦ ካላቸው የላይኞቹ ተፋሰስ ሃገራት መካከል ከኢትዩጵያ የሚሳው የዓባይ ወሃ ከ85 በመቶ በላይ/አልፎ አልፎም በዝናብ ወቅቶች እስከ 90 በመቶ ይደርሳል ተብሎ ይገመታል/ ድርሻ ያለው በመሆኑ የራሱ የሆነ የተለዩ ትኩረት መሳቡ አልቀረም፡፡ ዓባይ ለግብጽና ሱዳን ለዘመናት እየሰጠ ካለው ዘርፈ ብዙ ጥቅም አኳያ/በግብርና፤በሃይል ማመንጫ፤በማጠጥ ወሃ አቅርቦት፤በአሳ ሃብት፤በትራንስፖርት፤ በቱሪስት መስህብነት በወሃ ሳይንስ ምርምርና ኤንጂኔሪንግ/ ወዘተ ኢትዮጵያ አንዳችም ይህ ነው የሚባል ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች፡፡ ግብጽ በዓባይ ወንዝ ዳርቻዎች ላይና ከዚህ ጎን ለጎንም በማስኖ ከሦስት ሚሊዩን ሄክታር በላይ የሚሆነውን በረሃማ መሬት ለግብርና ሥራ በመጠቀም ህዝቧን ከዓመት ዓመት ያለአንዳች ችግር መመገብ ችላለች፡፡ በኢትዮጵያ የዝናብ እጥረት ኖሮ የዓባይ ወሃ መጠን በሚቀንስበት ጊዜ እንኳ ቢሆን፤ግብጽ በታላቁ የአስዋን ግድብ የተጠራቀመውን ወሃ በማስኖ በመጠቀም የግብርና ስራቸው ፈጽሞ ሳይስተጓጎል ሰብል የማምረት አቅማቸውን በከፍተኛ ደረጃ አጎልብተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአንጻሩ ከሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ሜሬት በላይ በመስኖ የሚለማ እምቅ አቅም ያላት ቢሆንም፤ ከዚህ ወስጥ እስካሁን በመስኖ ሚለማትና ጥቅም ላይ ማዋል የቻለችው ግን ከአምስት በመቶ በታች እንደሆነ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ በበርካታ ወስብስብ ሁኔታዎች፤ በአማዣኝም ውጫዊ ተጽእኖዎች ተጋርጠውባትና ከዚህም ጋር ተያይዞ በራሳችን በተፈጠረ የቁርጠኝነት ማነስ ብሎም የፋይናንስና ቴክኒካዊ የአቅም ወስንነት ምክንያት ሃገራችን ወሃወን ለልማት ለማዋል በእጅጉ ተቸግራ ኖራለች፡፡ እኛ ዜጎቿም በ"ዓባይን ልጅ ወሀ ጠማው" እንዲያም ሲል "ዓባይ ሚደሪያ የለው፤ ግንድ ይዞ ይዞራል" እና በሌሎችም የተረት ተረት አባባሎች ተደምሞን በርካታ የቁጭት ዘመናትን ለማሳለፍ ተገድደን ኖረናል፡፡ ይህ ሁኔታ በእርግጥም ቁጭት የሚያጭር ክስተት ሆኖ አሁን እስካለንበት ዘመን ደርሰናል፡፡

ይህን ታሪክ በወሳኝነት የሚቀይርና ከኢትዮጵያም አልፎ የውጭ ሃገራትንና ዓለም አቀፍ ታላላቅ ሚዲያዎችን ሳይቀር ያስደመመና ትኩረታቸወን የሳበ ታሪካዊ እርምጃ በቅርቡ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ተወስዷል፡፡ በኢትዮጵያ ህዝቦች የረጅም ዘመናት ታሪክ ያልተደፈረና ያልተሞከረ አኩሪ ታሪካዊ ክንወን በዚህ ትወልድ እወን ሊሆን እነሆ በዓባይ ላይ የሚገነባው የህዳሴ ግድብ ግንባታ በቅርቡ ተጀምሮ ስራው በመገፋፍ ላይ ይገኛል፡፡

የህዳሴ ግድብ ዓባይ ለኢትዮጵያም አንዱ ታላቅ የልማት ኃይልና የወደፊት ተስፋ ሊሆን እንደሚችል ያስማከረ እርምጃ በመሆኑም፤ ዜጎች የዓባይን ለልማት የማዋል ብስራት የተቀበሉት በታላቅ የደስታ ሲቃ ነበር፡፡ የግድቡ ፕሮጀክት ይፋ ከሆነበት እለት ጀምሮም በመላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድ የፈጠረው ከፍተኛ ስሜት፤ እልህ፤ ሃገራዊ መነሳሳትና ቁርጠኝነት ግለቱን ጠብቆ እየተጓዘ ይገኛል፤ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡ የግድቡ እወን መሆን የሚያስገኘው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታም ልማታችንን ወሳኝ ሊባል በሚችል ደረጃ በማፋጠን ረገድ ያለው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቀጣይ እድገቷን በኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ሴክተር ለመመስረት የነደፈችወን ስትራቴጂ ተፈጻሚ ለማድረግ ሰፊ የኃይል አቅርቦት መፍጠር ግድ ይላታል፡፡ ለዚህም የህዳሴው ግድብ እንዲያመነጭ የሚጠበቀው የ5 ሽህ 250 ሜጋ ዋት ኃይል ትልቅ ተስፋና አስተማማኝ መሰረት የሚጥር ታላቅ ሃገራዊ ፕሮጀክት ነው፡፡

ከኃይል ማመንጨት በተጓዳኝም በተወሰነ ደረጃ ለመስኖ ሥራ የሚጠቅም በመሆኑ ለግብርና ልማት የላቀ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ግድቡ የተፋሰሱንና የአካባቢውን ሥነ ምህዳር በአዲስ መልክ በማጠበቅና የሚለክአ ምድሩን ገጽታ በማለወጥ ረገድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ታላቅ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ በግድቡ በሚጠራቀመው ወሃ ወስጥም የአሳና ሌሎች የባህር ወስጥ እንስሳትን እንዲሁም አእዋፋትን ለመንከባከብና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ሁኔታን

ይፈጥራል፡፡ በሂደትም አካባቢውን ወደ ቱሪስት ማስህብነት በማለወጥ የቱሪስት ኢንዱስትሪውን በተወሰነ ደረጃ ለማዳገፍ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እንግዲህ የግድቡ ማሰራት በዋናነት ከታቀደለት ኃይል የማመንጨት ጠቀሜታው በተጓዳኝ ያሉት ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች በጥቅሉ ሲታዩ የግድቡን አስፈላጊነት በእጅጉ የሚያጎሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ግንባታው ሰፊ የህዝብና ዓለም አቀፍ ትኩረትን ሊስብ የቻለው፡፡

ህብረተሰቡ ግንባታውን በሁለንተናዊ መልኩና አቅም በፈቀደ ማጠን ለማዳገፍ ያለውን ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በተግባራዊ እንቅስቃሴ እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ በዚህም ማሰረት ሰራተኛው ከቦንድ ግዥ ጀምሮ በተለያዬ መልኩ የሚያደርገው አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ የወር ደሞዙን በራሱ ፈቃድና ተነሳሽነት ለማስጠት ቃል ገብቷል፡፡ ሌለው የህብረተሰብ ክፍልም በተለያዬ መልኩ የራሱን ሃገራዊና የዜግነት ድርሻ በሙሉ ፈቃደኝነት እንደሚያዋጣ ያለውን ዝግጁነት በተመሳሳይ መልኩ አረጋግጧል፡፡ ይህን ቃል ኪዳኑንም በተለያዩ አጋጣሚዎች በአንደበቱ እየገለጸ ይገኛል፡፡ ይህ ውሳኔ በግልጽ የሚያማለክተውም ዜጎች ለሃገራቸው ልማት ምን ያህል ቁርጠኝነት እንዳላቸውና መንግሥት በዚህ ረገድ ላደረገላቸው ሃገራዊ ጥሪ በራሳቸው አቅም ምን ያህል እርቀት እንደሚጓዙ ያስማለከረ አኩሪ የዜግነት ግዴታን የመወጣት ተግባራዊ ምላሽ ነው፡፡ ዜጎች በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረው ወቅታዊ የኑሮ ውድነትና የአቅም ውስንነት ሳይገድባቸው በነገ ሃገራዊ ልማትና እድገት ተስፋ ሰንቀው የገቡት ቃል ኪዳን የትውልድና የሃገር ኩራት ነው፡፡

ለመንግሥት ወቅታዊ ጥሪም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከዳር ዳር ተንቀሳቅሰው ተግባራዊ ምላሻቸውን በማስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ፕሮጀክቱ ይፋ በተደረገበት እለት ጠ/ሚኒስትር ማለስ ዜናዊ ግድቡን በመንግሥትና ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያ ሕዝቦች የራስ አቅም ለማንባት ማታሰቡንና ይህ እቅድ እውን እንዲሆንም፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ እምነት እንዳላቸው ገልጸው ነበር፡፡ አዎ- ዜጎች ይህን ጥሪ ከመነሻው ተቀብለው ነበር ብዙዎች እንደ አንድ ሆነው ታሪክ የጣለባቸውን የትውልድ አኩሪ ሃገራዊ ግዴታ ሊወጡ በጋራ ቃል የገቡት፡፡ ሕዝብ የሚፈልገውን የሚያውቅለትና በትክክል በአንድ የጋራ ሃገራዊ ዓላማ የሚሚራውና የሚያስተባብረው ካገኘ፤ ማንኛውንም አይነት እንቅፋት ታግሎ ለማለፍ እንደሚችል ያማለከተ፤የተናበበ የመንግሥትና የሕዝብ ፍላጎት የተንጸባረቀበትና ዜጎች ከምንጊዜውም በበለጠ ለልማት ያለቸው ቁርጠኝነት የተስተዋለበት በመሆኑ የግድቡ ግንባታ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሃገራዊ መግባባትን የፈጠረ ነው፡፡

ማሰረቱን በእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ባደረገውና ፍትሃዊነት በእጅጉ ከሚጎድለው ከዓባይ ውሃ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በተፋሰሱ ሃገራት መካከል በተለይም በአንድ በኩል በላይኛው የተፋሰሱ ሃገራትና በሌላኛው ወገን በግብጽና በሱዳን (Up-stream and Down-stream

Countries) ተብለው በሚጠሩት ሃገራት መካከል በይበልጥም ከግብጽ ጋር ያለው ግንኙነት በማጠራጠርና በስጋት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል፡፡ ይህም በተፋሰሱ ሃገራት የወሃ ፖለቲካ (Hydro-Politics) የዘመናት ማጋገሪያ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ አሁን እስካለንበት ጊዜ ዘልቋል፡፡ በዓለም ካሉ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች መካከል የዓባይ ተፋሰስ በርካታ ሃገራትን ያቀፈ ቀዳሚውና ረጅሙ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የላይኛው የተፋሰሱ ሃገራት ከምንም በላይ የወሃው ሕጋዊና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውና የጋራ ባለቤትነታቸው እንዲረጋገጥ ካላቸው ፍላጎት ጋር ተያይዞ ለረጅም ዘመናት የፍትሃዊነት ጥያቄ ሲያነሱ ቆይተዋል፡፡ በዚህ የግብጽ ፍጹም የበላይነት በሰፈነበት የዓባይ ወሃ አጠቃቀም ዙሪያ የላይኞቹን የተፋሰሱ ሃገራትን ያላሳተፈው/የሚያወክለው/ የቀደሞዎቹ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ስምምነቶች በተለይም (እኤአ የ1929 እና የ1959) ወሎችና ይህን ተከትሎ የሰፈነው ፍትሃዊነት የጎደለውና አድሎአዊነት ያለው አሰራር እንዲስተካከል ለማድረግ ሃገራችን ጠንካራ የሚነት አቋም ይዛ በሰላማዊና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ በስፋት ተንቀሳቅሳለች፡፡

ያም ሆኖ ግን ግብጽ በመካከለኛው ምስራቅና በይበልጥም ከእስራኤልና ከአረቦች ፖለቲካዊ ፍጥጫ ጋር በተያያዘ በምታራምደው ለዘብተኛ አቋምና በአረብ ሃገራት ዘንድ ያላትን የሚነት ሜና ተጠቅማ በምእራቡ ዓለም ባገኘችው ሰፊ ተደማጭነትና ድጋፍ ሳቢያ፤በዓባይ ጉዳይ ላይ የሚነሳው አጀንዳ ሁሌም ወደ እርሷ ተጠቃሚነት ብቻ እንዲያጋድል ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በርካታ የግብጽ ከፍተኛ ምሁራን በታላላቅና ዋና ዋና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወስጥ ተቀጥረው የመስራት ሰፊ እድል በማግኘታቸው በሚሰሩባቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት በስተጀርባ ሆነው ቀጥተኛና ስወር ተጽእኖዎችን ለመፍጠር አጋጣሚውን ተጠቅመውበታል፡፡ እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች በመኖራቸውም በየጊዜው የተነሱ የግብጽ መሪዎችና ምሁራን የላይኞቹ የተፋሰሱ ሃገራት በይበልጥም ኢትዮጵያ ፍትሃዊ የወሃ ድርሻቸውን ለልማት እንዳያወሉ ግለጽና ስወር ጫናዎችን በመፍጠር የውጭ ብድርና ትብብር እንዲነፈጋቸው በማድረግ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ የላይኞቹ የተፋሰሱ ሃገራት ከወሃው የማጠቀም ሕጋዊ መብት እንዳለቸው ታወቆ ጥያቄው እወቅና እንዳይሰጠውና ቢያንስ ቢያንስ እንኳ በመርህ ደረጃም ቢሆን ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ እንዳያገኙ የተለያዩ ተጽእኖዎች ሲደረጉባቸውም ቆይቷል፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የተፋሰሱ ሃገራት በራሳቸው የቴክኒክና የፋናንስ አቅም ወሃወን ለሚልማት የአቅም ወስንነት ያለባቸው መሆኑን ተከትሎም ለዘመናት የበይ ተመልካቾች ሆነው ቆይተዋል፡፡

የህዳሴ ግድቡን በራሳችን አቅም መስራት እንደምንችል ቁርጠኝነታችንን ሚጋገጣችንና ይህንንም መተግበር መጀመሯችን ብቻ በራሱ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ይከፍታል፡፡ ይህም የዚህ እድለኛ ትወልድ የታሪክ አሻራ ሆኖ በቀጣዮቹ የሃገሪቱ ትወልዶች ምንጊዜም ሲዘከር የሚኖር ታሪካዊ ክንወን ሆኖ

ሲታወስ የሚኖር ነው፡፡ ግንባታው መጀመሩ የሰበረውም ይህንን የ"አይችሉም፤አይሆንላቸውምና አይሞክሩትም" አመላካከትና አስተሳሰብ በመሆኑ ለሃገራችንና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ታላቅ ድል ነው፡፡ ዜጎች በአንድ ድምጽ ሆነው ግንባታውን በሁለንተናዊ መልኩ ለመደገፍ ያነሳሳቸው ጉዳይም በዋናነት ግንባታው ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ፈጥነን ለመውጣት በምናደርገው ጥረት ያለውን ወሳኝ ድርሻ በማንዘብ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም ቢያንስ ቢያንስ አሁን ባለንበት ሁኔታ የዚህ ዓይነት እጅግ ግዙፍ ግንባታ በራሳችን ተነሳሽነትና አቅም ለማድረግ እንደማንችል ተደርጎ ግብጽን ጨምሮ በሌሎች ወገኖች ዘንድ የተያዘውን ዘመን ተሻጋሪ የተሳሳተ አቋም ያፈረሰ የጽናታችንና የቁርጠኝነት ምልክት በመሆኑ ነው፡፡

ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ካላቸው ገቢ ቀንሰው ግንባታውን ለመደገፍ ያሳዩት የራስ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በእጅጉ የሚያኮራና የሚያስማሰግን ከመሆኑም በላይ ከዚህ ሕዝባዊ ማሳሳት በስተጀርባ አንዳንድ ጸረ ልማት ኃይሎች ሲያናፍሱት የነበረውን አሉባልታና በፌዝ የታጀለ የእንቶ ፈንቶ ሚዲናቆሪያቸውንና አጓጉል ስላቃቸውን እርቃኑን ያስቀረ ነው፡፡ የዓባይ ጉዳይ ሊያፌዙበት፤ሊዘባበቱበትና አሉባልታ ሊነገርበት ባልተገባ ነበር፤ ከነዚህ ኃይሎች ያየነው ግን ይህንኑ አሳፋሪ ድርጊት ነው፡፡

ኃላፊነት የጎደለውና ሃገራዊና የዜግነት ስሜት ብሎ ነገር በአጠገቡ ያላለፈ ማዛላበድና ማዛባበት የሞላበት ነወረኛ አባባሎችን በአንዳንድ የግል ጋዜጦች ላይ ማሰንዘራቸው እውን ይህ አመላካከታቸው ወይም አቋማቸው የኢትዮጵያን ሕዝቦች ያስደስታል ብለው ነው? ወይስ ሌላ ማንን ለማስደሰት ነው በዚህ ጊዜ ይህን እያሉ ያሉት? ብሎ ማጠየቅ ትክክለኛ ማንነታቸውን በግልጽ ለሚረዳት ያስችላል፡፡ የሆነ ሆኖ እነሱ ያውሩ፤ሕዝብ ግን ከምን ጊዜውም በበለጠ ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት ሃገሩን ሚልማዙን ይቀጥላል፡፡ የሚገርመው ግን እነዚህ አሉባልተኞችና አፍራሽ ኃይሎችም እንደሌላው ለልማቱ የቻለውን ያህል ሁለንተናዊ አስተዋጽኦና ድጋፍ ከሚያደርገው ህብረተሰብ ጋር ዘወትር ከሚያጥላሉትና ቢያንስ እንኳ እወቅና ከነፈጉት ሃገራዊ የልማት ትሩፋት እኩል ተጠቃሚዎች ሆነው መሜልከታችን ነው፡፡ እዚህ ላይ ከተገኘው ልማት ለምን ተጠቀሙ የሚል ጥላቻ በግሌ የለኝም፤ሆኖም ግን ከዚህ ትምህርት ወስደው ከስህተታቸው ሊታረሙ በሃገራዊና በዜግነት መንፈስ ኃላፊነት ሊሰማቸው ይገባል ባይ ነኝ፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን አንዳንዶች ቢያንስ ቢያንስ እንኳ ራሳቸውን ጨምሮ ዜጎችን ተጠቃሚ እያደረጋቸው ያለውን ልማት አምነው ለመቀበል ምንጊዜም የሚፈልጉ አይመስሉም፡፡ ለአሁኑ ጉዳያችን ይህን ነጥብ እዚህ ላይ በዝርዝር ማንሳት አስፈላጊ አይመስለኝም እንጂ፤ይህ ለምን እንደሆነ ደግሞ ትክክለኛ ምክንያታቸውን እነሱም ሆኑ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል በሚገባ ያውቁታል፡፡

በሌላ በኩል ግን የሕዝብ ልጆች በዓባይ ላይ ግንባታው ለተጀሚረው ለታላቁ የህዳሴ ግድብ አቅማቸው የሚችለወን ሁሉ ድጋፍ ለማስጠት በቁርጠኝነት እንደሚንቀሳቀሱ በተግባር እያረጋገጡ ለሚሆናቸው የእለት ተእለት ክስተት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ዜጎች በመንግሥት የቀረበላቸወን የልማት ጥሪም በታላቅ ሃገራዊና የዜግነት ስሜት ተቀብለው እስከሚጨረሻው ጫፍ እንደሚጓዙ እያረጋገጡ ይገኛሉ፡፡ መንግሥትና ሕዝብ አንድ ቋንቋ በመናገር ለልማት ያላቸወን ቁርጠኝነትና የዓላማ አንድነት በድጋሚ ያስማከሩበት ታላቅ ሃገራዊ ፕሮጀክት በመሆኑም፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከጫፍ ጫፍ በአንድነት ያስተሳሰረና ቃል ኪዳን ያስገባ በመሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

ደመወዛቸወን ለታላቁ የህዳሴ ግድብ የለገሱ የመንግሥትና የግል ሠራተኞች ያበረከቱት ገንዘብ በቦንድ ግዥ ሜልክ በየስማቸው የባንክ ሂሳብ ተከፍቶላቸው እንደሚያዝላቸው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት በቅርቡ ይፋ አድርጓል፡፡ ይህም በእወነቱ የወር ደሞዙን በራሱ የግል ተነሳሽነት በስጦታ ሜልክ አበርክቶ በነበረው ዜጋ ዘንድ ትልቅ ስሜት የሚፈጥር ነው፡፡ ምክንያቱም መንግሥት ይህን ያደርጋል ወይም ሰራተኛው ገንዘቡን በነጻ በማለገሱ ከገንዘቡ ሌላ ተጓዳኝ ጥቅም ወይም ትርፍ አገኛለሁ ብሎ አስቦ ያደረገው ስላልነበር፤ የምክር ቤቱ ወሳኔ በሌላ ሜልኩ ሰራተኛወን ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚያደርገወንና ያላሰበወን ተጨማሪ ጥቅምና ትርፍ የሚያስገኝለት መሆኑን በሚያዳቱ ነው፡፡ በማስረቱ መንግሥት በተጠና አካሄድ ይህን ወሳኔ ማስተላለፉ ለዜጎች እጥፍ ድርብ ጥቅም የሚያስገኝላቸው በመሆኑ የሚያስማሰግነው ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ግን የቁጠበ ባህል ባልዳበረበትና ከሌሎች በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ይገኛሉ ከሚባሉ አንዳንድ ሃገራት ጋር እንኳ ሲነጻጸር የቁጠበ ባህላችን እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደመገኘቱ፤ ይህ የመንግሥት እርምጃ ቁጠበን በማበረታታት ረገድ ስልታዊ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ ዛሬ ዜጎች በቁጠበ ሜልክ የሚያስቀምጡትና ለጊዜው የሚይጠቀሙበትን የባንክ ተቀማጭ ገንዘብ መንግሥት ለወቅታዊ የግንባታ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ሊጠቀምበት የሚያስችለወን ሰፊና አስተማማኝ እድል የሚፈጥርለት በመሆኑ ልማትን በራስ አቅም ለማፋጠን የሚኖረው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡ እዚህ ላይ የዜጎች ተጠቃሚነት ዘርፈ ብዙ መሆኑን በጥቂት ቀላል ምሳሌዎች ማዬት ይቻላል፡፡

ዜጎች የቁጠበ ባህላቸወን በማዳበር ከዚህ በሚያፈሩት ሃብት ለራሳቸው የሚጠቅም ተግባር ይከወኑበታል፤ መንግሥትም በቁጠበ የተጠራቀመወን ገንዘብ በፋይናንስ ምንጭነት ተጠቅሞ ወቅታዊ የልማት ፕሮጀክቶችን ያስፈጽምበታል፤ ከዚህ የመንግሥት ጥረትና እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞም በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በሚፈጠሩ የስራ እድሎች ዜጎች ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ የዚህ ድምር ወጤትም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል መንግሥት ከሚያስፈጽማቸው የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች እንደ ዜጋ

ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ ይህ ሂደትም ሃገራዊ እድገትን እውን በማድረግ ፍጥነቱን በአስተማማኝ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል አቅምን ለመፍጠርና ለማጎልበት ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቁጠባ ባንክ የሚቀመጠው የቦንድ ገንዘብ በአስፈላጊው ጊዜ ብቻ ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያነት በመንግሥት አማካይነት ወጪ እስከሚሆንበት ወቅት ድረስ በባንኮች እጁ ስለሚቆይ፤ በገበያው ውስጥ ያለውን የገንዘብ ስርጭትና ዝውውር በተወሰነ መጠንና ደረጃ ይቀንሰዋል፡፡ ይህም የዋጋ ግሽበትን ለሚገብ የራሱ የሆነ መጠነኛ አስተዋጽኦ እንዳለው የኢኮኖሚ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ የዋጋ ግሽበትን በተወሰነ ደረጃ ለመቀነስና ብሎም ሃገራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ከሚረዱ ዘዴዎች መካከልም ቁጠባ አንዱ እንደሆነ እዚህ ላይ በግልጽ መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ለህዳሴ ግድብ ማስፈጸሚያ በቁጠባ መልክ የሚካሄደው የቦንድ ሽያጭም እነዚህን የመሳሰሉ ተጓዳኝ ጥቅሞች ያሉት በመሆኑ ሃገራዊ ፋይዳው የላቀ ነው፡፡

ይህ የመንግሥት ውሳኔ በአንድ ወጥ በመላ ሃገሪቱ አዲስና ታሪካዊ የቁጠባ ባህል የሚፈጥር በመሆኑ፤ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከህዳሴው ግድብ ጋር የቀረበላቸው እጅግ ዋጋ ያለው ስጦታ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ የህዳሴው ግድብ ከሚያስገኘው ከፍተኛ ተጠቃሚነትና ግንባታው ካለው ሃገራዊ ፋይዳ በተጨማሪ ዜጎች በቁጠባ የሚያገኙት ተጠቃሚነትና በዚህ ረገድም የሚፈጠረው አዲስ የቁጠባ ባህል የዜጎችን ተጠቃሚነት እጥፍ ድርብ ያደርገዋል፡፡ ይህ ባህል ይበልጥ እየጎለበተ ሲሄድም ተመሳሳይ ሃገራዊ ፕሮጀክቶችን በአማዝኙ በራስ አቅም የማሰራት ልምድን የሚያዳብር መሆኑም ሌላው ታላቅ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ ዜጎች በዚህ መልኩ የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረጉም በቀጣይ ይበልጥ ለመቆጠብ የሚያነሳሳቸው እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ዜጎች ይበልጥ በቆጠቡ መጠንም ተጠቃሚነታቸው እየሰፋ መሄዱንና በቁጠባ ያስቀመጡት ገንዘብ ለሃገራዊ ልማት መዋሉ የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለው እየተገነዘቡ ስለሚሄዱ፤ በፕሮጀክቶች ላይ የባለቤትነት መንፈስ እያጎለበቱ ይሄዳሉ፡፡ ይህም ሃገራዊ ልማትን በሁለንተናዊ መልኩ ለመደገፍ ያላቸው ተነሳሽነት ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ዛሬ የምንቆጥበው ገንዘብ በቀጥታ ከሚያስገኝልን ተጠቃሚነት ባለፈ የሃገርን ኢኮኖሚ ለመደገፍ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አምነን እየታዬ ያለው ሰፊ ሕዝባዊ መነቃቃትና ተነሳሽነት ቀጣይነቱን ጠብቆ እንዲጓዝ ሁላችንም እንረባረብ የሚለው የዛሬው መልእክቴ ነው፤ ቸር እንሰንብት፡፡